# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

## የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት

ሰኔ /2017

ኢ.ግባ/ አዲስ አበባ/

**ደርሞ**

*የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በሁለት ዋና ዋና የቁጥጥር ፕሮግራሞች ማለትም በዕጽዋት ቁጥጥር ዘርፍ እንዲሁም በእንስሳት ቁጥጥር ስር ባሉ ክፍሎቹ የተደራጀና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚሄድ የቁጥጥር ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን ከነዚህ ዘርፎች በተጨማሪም የግብርና ሜካናይዜሽን ፣ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስራ ለማስጀመር እየሠራ ይገኛል ። ይህ የሪፖርት ሰነድ በተለይም የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ መሠረት ባደረጉ የቁልፍ ተግባራት አመልካቾች ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ የሪፖርት አጠቃላይ የግብርና ሴክተር ሪፖርት አካል ሲሆን በሁሉም ዘርፍ ታቅደው  በ2017 በጀት ዓመት የተከናወኑ ቁልፍ አመልካች አፈጻምን የሚያሳይ ነው። ለአብነትም አበይት ከሆኑ ክንውኖች መካከል የአበባን እርሻ ወደ ዓለማቀፍ ስታንዳርድ ለማስገባት እየተከናወኑ ያሉ የክትትል ስራዎች፣ የምርቶችን ጤንነትና ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ የተክናውኑ ተግባራት ይጠቀሳሉ። በክንውን ወቅትም፣ የበጀት እጥረት ፣ የተሽከረካሪና ሌሎችም ችገሮቸ ያጋጥሙ ሲሆን በአፈጻጸም ሪፖርቱ መሠረት በማድረግ ታቅደው የተከናወኑትን ቁልፍ  ሥራዎችን በሁሉም ዘርፎች በየድርሻቸዉ በዝርዝር ቀርቦ ዉይይት የተደረገበት ሲሆን የነበሩ ጠካራ ጐኖችን አጠናክሮ በመቀጠል ፣የታዩ ክፍተቶች ላይ በቀጣዩ በጀት ዓመት ትኩረት ሰጥቶ በመተግበር የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ ከዚህ በላቀ ሁኔታ የሚከናወን ይሆናል።*

## ማውጫ

1. መግቢያ ........................................ 3
i. የሪፖርቱ አስፈላጊነት ........................................ 4
ii. የሪፖርቱ መነሻ ........................................ 4
iii. የባለሰለጣኑ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች ........................................ 4
2. የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 የ12 ወር አፈጻጸም በቁልፍ አመልካች ........................................ 7
2.1 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴሽን እና መካናይዜሽን ሬጉሊቶሪ ........................................ 7
የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ማጠናከር ........................................ 7
2.2 የእጽዋት ግብዓቶች ምርቶች እና start-ups አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር ........................................ 8
የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ቁጥጥር ........................................ 8
ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች ........................................ 9
የእፀዋት ዝርያ ጥበቃና ዘር ጥራት ቁጥጥር ........................................ 10
2.3. የእንስሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር ........................................ 12
2.3.1 የእንሰሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ ........................................ 12
2.3.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ወደ ውጭ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ........................................ 14
2.3.3 የእንሰሳት መድሃኒት ጥራት ደህነነትና ፈዋሽነነት ማረጋገጥ ........................................ 14
2.3.4 ጥራትና ደህነነቱ የተረጋገጠ የእንሰሳት መኖ ........................................ 17
2.3.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንሰሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት ........................................ 19
3. በ2017 በጀት ዓመት የነበሩ ዕድሎችና ያጋጠሙ ችግሮች ........................................ 20
3.1 የነበሩ ዕድሎች ........................................ 20
3.2 ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ........................................ 20
4. በ2017 በዘርፉ በሁለተኛው አገር በቀል ሪፎርም የተለዩ የሪፎርም ተግባራት አፈጻጸም በግብርና ቁጥጥር የተደረጉ አስተዋጽኦ ........................................ 21
4. የ2017 የ4ኛው ሩብ ዓመት የበጀት አፈጻጸም ........................................ 22
የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 የ12 ወራት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በቁልፍ አመልካች ........................................ 23

# 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2017 በጀት ዓመት ያቀዳቸውን ቁልፍና ዝርዝር ተግባራት በዕቅዱ መሰረት ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ የባለስልጣኑ የዕቅድ ስርዓት በመካከለኛ ዘመን የግብርና ሴክተር በያዘው ዕቅድ መሠረት በማድረግ የሚከናወኑና በ4 ፕሮግራሞች ፣በ9 ስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም እነዚህን ስትራቴጂክ አላማዎች ለማሳካት በሚከናወኑ 39 ቁልፍ አመልካቾች የተመሠረተ ነው ፡፡ ባልስልጣኑ የዕቅዱን ተግባራዊነት ለመከታተል የሚያስችሉትን የተለያዩ ስልቶችን የሚጠቀም ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱና ዋናው የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ማሻሻል አንዱ ነው፡፡ በዚህም መሠረት፣ በበጀት ዓመቱ በ2017 በጀት ዓመት የተከናወኑትን ስራዎች በቁልፍ አመልካች በማቅረብ ይህ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ መሠረት የነበሩትን የአፈፃፀም ጥንካሬዎች ለማስቀጠል እና ክፍተቶችንም በመለየት የማሻሻያ ስራዎችን ለማከናውን ይረዳ ዘንድ በፕሮግራሞች በስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም በቁልፍ አመልካቾ ላይ መሠረት ባደረገ መልኩ የ2017 በጀት ዓመት ሪፖርት እንደሚከተለው አቀርቧል፡፡

## i. የሪፖርቱ አስፈላጊነት

የኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን በየጊዜው ሊለካ የሚችል ግብ በማስቀመጥ በ10 አመት እንዲደርስበት የታቀደው ግብ ላይ ለመድረስ በየአመቱ ዕቅዱን ሊፈጸም በሚችልና አሳታፊ በሆነ መልኩ አቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል በዚህም መሠረት ፦

- በሩብ አመቱ የታቀዱ ሥራዎችን የሚገመግምበትና ባለሰልጣኑ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ
- በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለመለየት፣
- የእርስ በርስ መማማር ለመፍጠርና ለባለድርሻ አካላት ወቅታዊና ተገቢ የሆነ መረጃ ለመሰጠት ነው።

## ii. የሪፖርቱ መነሻ

ባለስልጣኑ በ2018 በጀት ዓመት ላስቀመጠው ግብ ስኬት እንደመርህ የያዘው ከዚህ በፊት ያጋጠሙ ችግሮችና እና መልካም እድሎችን በሚገባ በመፈተሽ፣ ዕቅድን አሳታፊ በማድርግ፣ ሪፖርቶች ግልጽ እና ዉጤታማ እንዲሆኑ ሲሆን ይህ ሪፖርት በዋናነት እንደመነሻ በማድረግና በዋናነት በቀጣዮቹ ጉዳዮች ላይ መሠረት በማድረግ ሲሆን እነዚህም፦

- የግብርና ሚኒስቴር የ10 አመት እና የመካከለኛ ዘመን እቅድ
- የባለስለጣኑ የ2017 በጀት አመት እቅድ እንዲሁም
- የባለስልጣኑን የ2017 1ሩብ እና 2 ሩብ  አመት 3 ሩብ አመት አፈጻጸም ሪፖርት ናቸው።

## iii. የባለሰለጣኑ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶቸ

**ተልዕኮ**

- የግብርና ቴክኖሎጂ፣አገልግሎቶችን ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ደህንነት፣ፍቱንነት፣ ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤መልካም ስም ያለውና ፣ ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓትን በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የግብርና ምርቶችን የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት።

## ራዕይ

- በአለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም መሆን

## እሴቶች

- ታማኝነት /Loyalty/
- ሚስጥር ጠባቂነት /Confidentiality/
- አገልጋይነት /Commitment/
- የህግ የበላይነት /Rule of the law /
- ተጠያቂነት /Accountability /
- ደንበኛ ተኮር አገልግሎት /Customer focus/
- አለማዳላት /Impartiality /
- ትብብር /Partnership /
- ግልጽነት /Transparency/
- ምላሽ ሰጪነት /Responsiveness/

## የባለስልጣኑ ስትራቴጅክ ግቦችና/ፕሮግራሞች

ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ

ቁልፍ ተግባራት

- ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ
- በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

የእፀዋት በዕጽዋትና ፣ከእፀዋት ጋር በተገናኙ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ማጠናከር

- ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ
- ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች
- የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር
- ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶነሪ አገልግሎት

የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከር

- የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ
- በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች
- ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት
- ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ
- ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት

ተቋማዊ የመፈፀም አቅም ግንባታ፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ እና የህግ ማዕቀፎች

- የአቅም ግንባታ ሥራዎች
- የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ማሻሻል
- የሃብት አጠቃቀምን ማሳደግ እና ሃብት ማፈላለግ
- የእቅድ ክትልና ግብረ መልስ ሥራዎችን ማከናወን
- ተቋማዊ አገልግሎትን ማሻሻል
- ሥርዓተ ጾታና ማህበራዊ አገልግሎት መተግበር
- ተቋማዊ ዲጅተላይ"ዘሽን አገልግሎት መስጠት
- ተቋማዊ ሪፎርም አተገባበር
- አጋርነት እና ህዝብ ግንኙት
- ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና

## 2. የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 የ12 ወር አፈጻጸም በቁልፍ አመልካች

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የዕቅድ ስርዓት በመካከለኛ ዘመን የግብርና ሴክተር በያዘው ዕቅድመሠረት በማድረግ የሚከናወኑና በ4 ፕሮግራሞች ፣በ9 ስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም እነዚህን ስትራቴጂክ አላማዎች ለማሳካት በሚከናወኑ 39 ቁልፍ አመልካቾች የተመሠረተ ነው ።ይህንን መሠረት አድርጎም የባለስልጣኑ የ2017 ሪፖርት በፕሮግራሞች በስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም በቁልፍ አመልካቾ ላይ መሠረት ያደረገ ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 2.1 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴሽን እና መካናይዜሽን ሬጉሊቶሪ

**የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ማጠናከር**

**ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ**

- የስራ ዘርፉ አዲስ የተደራጀ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የሬጉላቶሪ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል የቅድመ-ዝግጅት ስራዎችን ማከናወኑ ወሳኝ በመሆኑ ሁለት የአሰራር መመሪያዎችን ረቂቅ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፣
    - ✓ ረቂቅ መመሪያዎቹን በጋዜጣ እና በድረ-ገጽ ለሕዝብ አስተያየት እንዲቀርቡ በማድረግ አስተያየቶች ተሰብስበዋል፣
    - ✓ በረቂቅ መመሪያዎቹ ላይ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማቅረብና በማስተቸት አስተያየቶች ተሰብስበዋል፣
    - ✓ የመመሪያዎቹን ረቂቅ ሰነዶች ላይ የማስተካከያ ስራዎች በመከናወን ላይ ሲሆን ለሚመለከታቸው በማቅረብና በማስተቸት እንዲጸድቁ ይደረጋል፤
- በብሔራዊ የግብርና ሜካናይዜሽን ፎረም፣ እንዲሁም በሶስት ክልሎች ማለትም በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ እንዲሁም በአማራ ክልል የግብርና ሜካናይዜሽን ፎረሞች ላይ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዓላማ፣ ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም በረቂቅ ደረጃ የሚገኙትን መመሪያዎችን በሚመለከት ለፎረሙ ተሳታፊዎች ገለጻና ማብራሪያ ተደርጓል፤
- በብሔራዊ ደረጃ በመዘጋጀት ላይ ባለው ባለብዙ ተዋንያን ኤክስቴንሽን አዋጅ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፤ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት የቁጥጥር የህግ ማዕቀፍ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ ተደርጎ የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል፣
- በመዘጋጀት ላይ ባለው የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማሻሻያ ደንብ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፤ የግብርና ምርምር የቁጥጥር አሰራር መመሪያ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ ተደርጎ የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል፣

- በሜካናይዜሽን አገልግሎት አሰጣጥና የቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ላይ አንድ ሰው እንዲሰለጥን ተደርጓል፤
- የስራ ዘርፉ አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ የሚሆኑበትን አሰራር ለመዘርጋት ሁለት ሰዎች በኢ-ሰርቪስ ላይ እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፤
- በሀገር ደረጃ የተፈጠረውን መልካም ዕድል በመጠቀም በኢ-ኮዲንግ ስልጠና በመሳተፍ ሁለት የክፍሉ ሰራተኞች ሰርቲፊኬት አግኝተዋል፡፡

## 2.2 የእጽዋት ግብዓቶች ምርቶች እና start-ups አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር

### የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ቁጥጥር

### ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ ተባይ

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ለ111437 ሚትሪክ ቶን ፀረ ተባይ የመግቢያ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ111237 ሜትሪክ ቶን ፀረ ተባይ የፍቱንነት፣የደህንነትና የጥራት ማረጋገጥ ስራዎችን በማከናወን  የመግቢያ ፍቃድ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም 99.8% ነው፡፡

### ጥራቱ የተረጋገጠ ማዳበሪያ

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ለ2339971 ሚትሪክ ቶን ፀረ ተባይ የመግቢያ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ2030774 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ የጥራት ማረጋገጥ ስራዎችን በማከናወን የመግቢያ ፍቃድ የተሰጠ  ሲሆን አፈጻጸሙም 86.9%  ነው፡፡

### የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ለ225 አዳዲስ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ተቋማት በምዝገባ መስፈርቱ መሰረት መመዝገብ እና የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ 231 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ+100% በላይ ሆኗል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞም

### በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ  ሁለት  በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ የሚያስችሉ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ  ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

### የፀረ-ተባይ ኢንስፔክሽን ሥራና ግኝቶች

- የፀረ-ተባይ አስመጭዎች፡ ችርቻሮ ነጋዴዎችና ተጠቃሚዎች አጠቃላይ **34** ድርጅቶች ላይ ኢንስፔሽን በማድረግ ሙያዊ ድጋፍ የመስጠትና እንዲሁም ችግር

ያለበቸዉ ላይ የማስተከካያ ሀሳቦች የተሰጠ ሲሆን አጠቃላይ የታዩ ችግሮች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል፡-

ፓሌቶች አጠቀቃም

- የእሳት አደጋ መከላከያ በአንዳንድ የፀረተባይ መጋዘኖች አንዳንዶች የማይሰሩ ሆኖ መገኘታቸው፤
- መጋዘኖች መስኮቶች ዝግ በመሆናቸው በቂ የአየር ዝውውር ችግር መታየት፤
- የሰራተኛ ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች እጥረት፤
- የፀረተባዮች አደራደር ችግር፣
- የአደገኛ ምልክቶች በሁሉም መጋዘን ላይ አለመታየት እና የሰራተኞች ደህንነትንና እነዚህ ችግሮች ለማሻሻል ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡

## ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች

- በ2017 በጀት ዓመት ወደ ዉጪ ሀገር ለሚላክ የጥራጥሬ እህሎች'የቅባት እህሎች' የብርዕ እና አገዳ እህሎች 'የቡና ምርት 'የአበባ ምርት' አትክልትና ፍራፍሬ ምርት' ቅመማቅመም ምርት እንዲሁም ሌሎች የግብርና ምርቶች ላይ ተገቢውን ኢንስፔክሽን ወይንም ምርመራ ለማካሄድ 860000 ቶን ታቅዶ ክንዉን 877750 ቶን (101%) ምርት ወደ ተለያዩ ሃገራት እንዲላክ ተደርጎል፡፡

## ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች

- ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች ላይ በ2017 በጀት ዓመት 60000 ቶን የኢንስፔክሽን ሥራ ለመስራት ታቅዶ ክንውን 87020 ቶን (>100 %) የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የተደረጓል፡፡ ለአፈጻጸም ከፍተኛ መሆን በልዩ ፈቃድ ለቢራ ፋብሪካ የገባው የገብስ ምርት መጠን ከፍተኛ መሆኑ እንዲሁም ቀደም ብሎ በአዳማ በኩል ፍራንክቫሎታ ተጠቃሚ ሆነናል በሚል የግንዛቤ ክፍተት የጉምሩክ ጽ/ቤት መልቀቂያ ሳይጠይቅ ምርቶችን እንዲገቡ ሲያደርግ የነበረዉ ክፍተት እንዲታረም በመደረጉ ሁሉም የፍራንኮቫሎታ ተጠቃሚ አስመጪዎች ያለ መልቀቂያ ፈቃድ እንዳይገቡ በመከልከላቸዉና ሁሉም መልቀቂያ ፈቃድ ወስደዉ ምርቶች መግባት በመጀመራቸዉ የመጣ ከፍተኛ ሪከርድ ነዉ፡፡

## የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች

በ2017 በጀት ዓመት  በገቢና ወጭ የግብርና ምርቶች ላይ የብቃት ማረጋጋጫ ለሚጠይቁ ተገልጋዮች የባለሙያ፣ የቢሮ፣ የመጋዘን ኢንስፔክሽን በማካሄድ እና ሌሎች መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው በማረጋገጥ በቁጥር 838 ለመስጠት ታቅዶ 611 (72.9%) የብቃት ማረጋገጫ  መስጠት ተችሏል::

## የእፀዋት ዝርያ ጥበቃና ዘር ጥራት ቁጥጥር

- ለ120 በምርምር የቀረቡ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎችን ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ 122 እጩ ዝርያዎች ቀርበው የተገመገሙ ሲሆን አፈጻጸሙም 100+% ነው አፈጻጸመሙ ከዕቅዱ በመጠኑም ቢሆን ከፍ ያለው በክልል የሚገኙ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከአቅራቢያ የምርምር ተቋማት ገምጋሚ ባለሙያዎችን በመጠቀም ስራው እንዲከናወን በመደረጉ ነው፡፡
- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ጥራትና ዉጤታማነታቸው ተረጋግጦ የተመዘገቡና የተለቀቁ የዕፅዋት ዝርያዎች 78 ታቅዶ 97 ከ100% በላይ ነው፡፡
- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ  በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ የአገር ውስጥ ዘር1,527,905 ታቅዶ 816,891የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 53.5%ነው፡፡ ሪፖርቱ የተቖጣጣሪ አካላት ያለቸውን 8 ክልሎች ብቻ የሚያጠቃልል ነው፡፡
- በቁጥር 250 ከውጪ የገባ ዘር ናሙና ጥራቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ ለማድረግ ታቅደ 420 የተከናውነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ+100% በላይ የሆነ ሲሆን ከፍ ያለበትም ምክንያት አስመጪዎች ዶላር በማግኘታቸው ማስመጣት በመቻላቸው ነው፡፡

- 509603 ኪሎግራም ከውጭ አገር ሚገባ የአትክልት ዘር በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 439,003 ኪሎ ግራም በቁጥጥር ስር ያለፈ ሲሆን አፈጻጸሙም 86.14 % ነው አፈጻጸሙም ዝቅ ያለት ምክንያት የናሙናዎቹ ወካይ መጠን ወይም lot size አነስተኛ ስለነበረ ነው ::
- ለ 30 አዲስ በዘር ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅደ ለ 31 አዲስ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ  የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

### የዕጽዋት ምርትና ግብዓት ላቦራቶሪ

- የእጽዋት ግብአትና ምርት ጥራትና ደህንነት ምርመራ ስራዎች በባህሪያቸው ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የስራ ክፍሉን ለመደገፍና በተሻለ ደረጃ ለማጠናከር የሚያስችል ተጨማሪ የበጀት (ፋይናንስ) ምንጮችን ለማፈላለግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ የፕሮጀክት ንድፈ-ሀሳብ ተዘጋጅተው ሀብት የማፈላለግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከዚህ ቀደም ከስራ ክፍሉ ጋር በጋራ እየሰሩ ከሚገኙ አጋር ድርጅቶች በተጨማሪ አራተኛ ሩብ አመትን ጨምሮ በዓመት ተጨማሪ ሀብት ለማፈላለግ ከሌሎች አጋዥ

ድርጅቶች ጋር (ማለትም ከፒቲቢ (PTB)፣ ከጂአይዜድና ከኤስ ኤን ቪ-ኢትዮጵያ) የስራ ግንኙነት ለመፍጠር ትልቅ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

- ለምግብ ጥራት እና ደህንነት ምርመራ ላቦራቶሪ ስራ አስፈላጊ የሆኑ በበጀት አመቱ ለማከናወን ከታቀደው ስድስት (6) የቅድመ የጥራት አስተዳደር ስርአት ትግበራ ሰነዶች ውስጥ የስድስቱም ረቂቅ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡
- የእጽዋት ዘር ፍተሻ ላቦራቶሪ የISTA የሶስተኛ ወገን አለም አቀፍ እውቅና (አክሪዲቴሽን) ሂደት በሶስተኛው ምእራፍ ላይ ከመገኘቱ ጋር ተያይዞ እንድናሟላ ወይም እንድናቀርብ በማህበሩ የተጠየቁ አስገዳጅ ሰነዶችን ጨምሮ በአራተኛው ሩብ አመት የስራ አጋራችን ከሆነው ከኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በዘጠና ሁለት (92) የላቦራቶሪ የጥራት አስተዳደር ስርአት ትግበራ ሰነዶች ላይ እና ተያያዥ አስተዳደራዊ የአሰራር ስርአት ሰነዶች ላይ የረቂቅ ዝግጅት ስራ ተጀምሯል፡፡
- የISTA አክሪዲቴሽን የምርመራ ወሰኖችን (Scope) በተለያዩ ዘርፎች የበለጥ ለማስፋት በዚህ አመት (2025) በሶስተኛው ዙር በአትክልት ዘር ላይ ISTA በአለም አቀፍ ደረጃ በሚሰጠው የፐሮፊሽንሲ ቴስት (ፈተና) በሁለት የምርመራ ስነ-ዘዴ አይነቶች (Parameters) የተሳተፍንና በፈተናውም ጥሩ የሆነ ውጤት የተመዘገበ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በሂደቱም በምርመራ ዘዴዎቹ ላይ የሶስተኛ ወገን አለም አቀፍ እውቅና (አክሪዲቴሽን) ጥያቄ ማቅረብ የምንችልበትን ውጤት ማግኘት ተችሏል፡፡
- የእጽዋት ዘር ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪን በአዲስ መልክ የማደራጀትና የማቋቋም ስራ በአራተኛው ሩብ አመት ከተከናወኑ ስራዎች መካከል አንዱ ነው፡፡
- ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በእጽዋት ዘር ጥራት ፍተሻ ላብራቶሪ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ የፍተሻ/የምርመራ መሳሪያዎችና ሌሎች ተያያዥ ቁሳቁሶች ላይ የትክክለኛነት ምዘና (ካሊብሬሽን (Calibration)) እና የማረጋገጫ ስራ በኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት አማካኝነት ተሰርቷል፡፡ በተያያዘም በኢንስቲትዩት ለመሳሪያዎቹ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል፡፡
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጉርድ ሾላ አካባቢ ባገኘው አዲስ ቦታ ላይ በአሁን ሰአት በእጽዋት ዘርፉ የምግብ ጥራትና ደህንነት ምርመራ/ፋተሻ አገልግሎት የሚሰጡ ሁለት (ማለትም፦ የኬሚካል ረሲጁ ምርመራ ላቦራቶሪ እና የማይኮቶክሲን ምርመራ ላቦራቶሪ) ላቦራቶሪዎችን የማቋቋም ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእፅዋት ላቦራቶሪ የምርመራ መሳሪያዎች፣ የላቦራቶሪ ሶልቨንቶች፣ ሪኤጀንቶች፣ ኪቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእፅዋት ላቦራቶሪ ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች መሟላታቸው ተረጋግጦ ለ1 ድርጅት የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ ተሰጥቷል፡፡
- በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለሚገኙ የተመረጡ የምግብ ጥራት እና ደህንነት ምርመራ እና የእጽዋት

ዘር ጥራት ምርመራ ስራ ለሚሰሩ ላቦራቶሪዎች በቦታው በመገኘት በላቦራቶሪ አስተዳደር ስርአት ላይ እና በተለያዩ በምርመራ ዘዴዎች ላይ የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

- ከፌዴራል እና ከተለያዩ የክልል ግብርና ቢሮዎች እና የግብርና ግብዓቶች እና ምርት ቁጥጥር ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ለተውጣጡ የእጽዋት ዘር የላቦራቶሪ አናሊስቶች እንዲሁም የስራ ሀላፊዎች በኢስታ (ISTA) የሶስተኛ ወገን እውቅና አሰጣጥ ስርአት ሂደት ላይ፣ በላቦራቶሪ የአስተዳደር ስርዓት ላይ እና በእጽዋት ዘር በሽታዎች ልየታ ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ የግብርናና የምርምር ባለሙያዎች የዘር ላብራቶሪ የአሰራር ስርአት እና የምርመራ ዘዴዎችን በተመለከተ የልምድ ልውውጥና ግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ተከናውኗል፡፡
- ኢትዮጵያ በሚገኘው ዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት (International Livestock Research Institute (ILRI)) በተደረገ ከፍተኛ ድጋፍ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ለሁሉም የእጽዋት ዘር ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ ባለሙያዎች እና የስራ ሀላፊዎች በእጽዋት ዘር ናሙና አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ በዘር ጤና ምርመራ፣ በዘር አጠባበቅ እና በሌሎች በተለያዩ የዘር ጥራት ምርመራ ስነ-ዘዴዎች ላይ የንድፈ ሀሳብ እና የተግባራዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## 2.3. የእንሰሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር

### 2.3.1 የእንሰሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

**ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽ አገልግሎት መስጠት፣**

- የቅድመ ዕርድና ድህረ እርድ ምርመራ በማከናወን እና የቄራዎችን ሀይጅንና ሳኒቴሽን እንዲጠበቅ በመቆጣጠር ጤንነቱ ፣ ደህንነቱና ጥራቱን የጠበቀ ለወጭ ገበያ የሚቀርብ እና ለሰው ምግብነት የሚውል የስጋ ምርት እንድመረት በማስቻል እንዲሁም በላቦራቶሪ ምርመራ የስጋ ደህንነት እንዲረጋገጥ በማድረግ 15000 ቶን ሥጋ እና ተረፈ ስጋ ምርት ወደውጭ እንዲላክ ታቅዶ በድምሩ 21200 ስጋ እና ተረፈ ስጋ ተልኳል አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

**ዓለም አቀፍ የሥጋ ደህንነት እና ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የስጋ ምርት ወደ ውጪ እንዲላክ ማድረግ፡፡**

- ለምርቶቹ የተሰጠ የደህንነትና ጤንነት ማረጋገጫ ሰረተፊኬት 5500 ታቅዶ 7320 ተሰጥቷል አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

## በእንስሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የተካሄደ  ኢንስፔክሽን

- በ56 ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ በ60 ተቃማት ላይ ተከናውኗል፡፡አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

**ጥራቱና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ የእንስሳት ምርት ናሙናዎች**

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ  600 የእንስሳት ምርት ናሙናዎች ላይ የፊዚኮ-ኬሚካል እና የማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ሥራዎች ለማከናወን ታቅዶ ከተለያዩ አከባቢዎች በተሰበሰቡ 709 የሥጋ እና የወተት ምርት ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ ሥራ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም(>100%) ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ፍተሻ ማካሄድ ተችሏል፡፡

**ለኮመርሻል የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ**

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ለ71 **የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች  የብቃት ማረጋገጫ** ለመስጠት ታቅዶ ለ72  **የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች  የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች**  የድጋፍና ክትትል ሰራዎችን በማከናወን ለመደገፍ ተችሏል አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

  በ12 ወር ውስጥ የኦድት ምርመራ የዓለም አቀፍ የምግብ ደህንነት ስርዓት (ISO 22000) /HACCP መስፈርት አሟልተው የተገኙ ኤክስፖርት ቄራዎች

  - በ11 ኤክስፖርት ቄራዎች የስጋ ምርት ተቀባይ አገራትን እና ዓለም ዓቀፍ የምግብ ደህንነት ስርዓት መስፈርቶችን አሟልተው የሚሰሩ መሆናቸውን 4 ኦዲት በማድረግ የምግብ ደህንነት የአሰራር ስርዓቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ታቅዶ 4 ተከናውኗል ፡፡
  - በ UNIDO ፕሮጀክት ድጋፍ 2 ቄራ በቻይና ሬጉላቶሪ አካል ግምገማ ተደርጎበታል ፤- የቻይና ኢንፖርት ኤክስፖርት አሶሴሽን ወደ ሀገራችን መጥተው በየምግብ ማቀነባበሪያ ተቋማት መሰረተ ልማት፤ፋሲሊቲ ላይ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም ወደ ቻይና ገበያ ለመግባት GACC questionnaire ተሞልቶ ወደ ግብርና ሚኒሰቴር ተልኳል፡፡
  - የስጋ ሴክተሩን ዲጅታላዝ ለማድረግ ሲስተሙ አልቆ ለባለሞያዎች በሰርቪስ ዲጅታላይዜሽን፣ኢ-ለርኒግ እና ዌብሳይት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - በእንሰሳት ጤና እና ደህንነት አዋጅ ላይ የኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን አሁን ባለው አደረጃጀት መሰረት እንዲቃኝ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡
  - ከዱባይ በመጡ ኦዲተሮች 3 ቄራዎችን ማስገምገም ተችሎ ጥሩ ግብረ-መልስ ተገኝቷል፡፡

### 2.3.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ወደ ውጭ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች

- በበጀት አመቱ አጠቃላይ 390000 ወደ ውጭ የሚላክ የቁም እንሰሳት/ዳልጋ ከብት፣ ግመል/ በግ፣ ፍየል/ በኳራንትን ጣቢያዎች ውስጥ በማቆየት አስፈላጊን ክትባትና የጤና ምርመራ በማድና ጥራቱና ጤንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 621000 የቁም እንሰሳት ጥራትና ጤንነቱን በማረጋገጥ ወደ ተቀባይ ሀገራት የተላከ ሲ"ሀን አፈጻጸሙም +100% ሆኗል።
- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ 546000 ወደ ውጭ የሚላክ የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ በማረጋገጥ ወደ ውጭ ለመለላክ ታቅዶ 476,4449 የለማ እንቁላይ በኳራንቲን ሰርትፊኬሽን በመስጠት እንዲወጣ የተረገ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ+100% በላይ ነው፡
- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ወደ ተቀባይ ሀገራት የማርና ሰም ምርት ለሚል ድርጅቶች የኢንስፔክሽን እንዲሁም የላብራቶሪ ምርመራ ተደርጐላቸው 450 ቶን ማርና ሰም ለመላክ ታቅዶ 270 ቶን የጤና አገልግሎት ሰርትፊ"ከሽን በመስጠት እንዲላኩ የተደረገ ሲሆን ይም አፈጻጸሙ 57.3% የሆነ ሲሆን አፈጻጸሙም ዝቅ ያለበት ምክንያት የሀገር ውስጥ ፍላጐት መጨመር እና የዋጋ ንረት መኖሩ ነው፡
- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ 3572450 ያለቀለት ቆዳና ሌጦ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ 4694016 የሳኒተሪ ሰርትፊኬት በመስጠት ከሀገር እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም +100% ሆኗል።
- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ለ689,090 ወደ ሀገር የሚገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 733,662 (›100%) ተከናውኗል
- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ለ 275 ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባ የተሸሸለ ዳልጋ ከብት ጤንነቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 793(+100%) በላይ ተከናውኗል።
- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ 12000 ወደ ዐገር ለሚገባ አባላዘር ጤንነቱ እና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 152,146 (+100%) በላይ ተከናውኗል።

## 2.3.3 **የእንሰሳት መድሃኒት ጥራት ደህነነትና ፈዋሽነነት ማረጋገጥ**

**ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት**

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ 2850 ቶን ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታቅዶ 3682.967 ቶን የእንስሳት መድኃኒት ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። አፈጻጸሙም +100% ሆኗል።

አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ተገልጋዮች አገልግሎቱን ፈልገው በብዛት ባመምጣታቸው ነው፡፡

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ 75 የእንስሳት መድሃኒት ለመመዝገብ ታቅዶ 190 የእንስሳት መድኃኒት እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም +100% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት መስፈርቶቹን ያሟሉ መድሃኒቶች በብዛት በመኖራቸው ነው፡፡ የሶስት መድሃኒቶች 15 ባች የላቦራቶሪ ውጤት አሴ ከደረጃ በታች በመሆኑ ምዝገባው እንዲቋረጥ ተደርጐል፡፡ የ 3 የምዝገባ መድሃኒቶች የላቦራቶሪ ውጤት ፒኤች ከተቀመጠው ስፔስፍኬሽን በላይ ወይም በታች በመሆኑ ምዝገባው እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡

**የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የተካሄደ የጥራት፣ ደህንነት እና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ**

- በበጀት አመቱ አጠቃላይ ከተገልጋዮች በሚቀርቡ 300 የመድኃኒት ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በ 377 (>100%) ናሙናዎች ላይ የጥራት ምርመራ ሥራዎችን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት**

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ለ375 የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንሰጣለን እናድሳለን ብለን አቅደን 389 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰቷል፡፡ አፈጻጸሙም +100% ሆኗል፡፡

**የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን**

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ ለ629 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን እናረጋለን ብለን አቅደን 559 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን አካሂደናል፡፡ አፈጻጸሙም 88.8% ሆኗል፡፡

በኢንስፔክሽን ወቅትም የታዩት ክፍተቶች እና የተወሰዱ እርምጃዎች፦-

- 7 ድርጅቶች በራሳቸው ፈቃድ ተሰርዘዋል፣ 25 ድርጅቶች በኢንሰፔክሽን ወቅት ክፍተት በመኖሩ እና በሰዓቱ ባለማሳደሳቸው ተሰርዟል፡፡

- አንድ አስመጪ የመጠቀሚያ ጊዜ አልፎባቸው የተከማቹ 428 ብልቃጥ ሆርሞን እንዲወገድ አድርገናል፡፡ ለተወገዱ መድሃኒቶችም ለሚመለከተው ክፍልም ማረጋገጫ ተጽፏል፡፡
- በመግቢያና መውጫያ ኬላ ላይ የጥራት ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ለተወሰደ ናሙና ከደረጃ በታች በመሆኑ 30¸000 ብልቃጥ አይቨርመክቲን የሚባል የእንስሳት መድኃኒት እንዲወገድ አድርገናል፡፡ ለተወገዱ መድሃኒቶችም ለሚመለከተው ክፍልም ማረጋገጫ ተጽፏል፡፡
- 2 ባች በተለያየ ጊዜ ወደ ሃገር ሊገቡ የነበሩ የእንስሳት መድኃኒቶች የመግለጫ ጽሁፍ (labeling) ችግር ስለነበረበት ከኬላ እንዳይለቀቅ ተደርጉል፡
- 247560 ሳቼት አሾክሲ 5 ግራም እና 9840 ሳቼት አሾክሲ 100 ግራም  በላብራቶሪ ውጤት መሰረት እንዲወገድ ኳራቲን ተደረጓል፡፡
- 4000 ቪያል አሽታይል 20%  በላብራቶሪ ውጤት መሰረት እንዲወገድ ኳራቲን ተደረጓል፡፡
- 2150 ቪያል አሾክሲ10%  በላብራቶሪ ውጤት መሰረት እንዲወገድ ኳራቲን የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- 240 ቪያል ኦክሲ10%  እና 41 ቪያል አይቨረመክቲን የተበላሸ በመሆኑ እንዲወገድ ተደረጓል፡፡ ለተወገዱ መድሃኒቶችም ማረጋገጫ ተጽፏል፡፡
- AVINEW NEW 10000000 ዶዝ ክተባት የተበላሸ በመሆኑ ከአምራቹ መረጃ ስለደረሰን  ለማስወገድ  የዶክመት ቬሪፊኬሽን ስራ ተሰርቷል፡፡
- CORYMUNE 7K ብዛቱ 200 000 የሆነ ክተባት የጥራት ችግር መኖሩ ከአምራቹ መረጃ ስለደረሰን እስኪጣራ ድረስ ኳራንቲን ተደረጎ እንዲቀመጥ ተደረጓል፡፡
- አሾክሲ 5 ግራም እና አሾክሲ 100 ግራም በላብራቶሪ ውጤት መሰረት ፒኤች የወደቀ ቢሆንም ባስመዘገቡበት BP ላይ የፒ ኤች ፓራሜትር  ስለማይጠይቅ እንዲለቀቅ ተደረጓ ፡፡
- 10 መድሃኒቶችን ናሙና በድህረ ገበያ ጥናት ወደ ላቦራቶሪ ያስገባን ሲሆን 8ቱ መደሃኒቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ሲሆን ሁለቱ መድሃኒቶች ግን ከተቀመጠው ደረጃ ውጪ በመሆናቸው ከገበያ እንዲሰበሰብ ደብዳቤ ለአስመጪዎቹ እና ለክልልች በደብዳቤ ያሳወቅን ሲሆን የመድሃኒቶቹን የምዝገባ ሰርትፊኬቶች እንዲሰረዙ አድርገናል፡፡
- አምስት ለምዘገባ የተላከ መድሃኒቶች ከተላከው ወጤት ፒ ኤች ያላሟሉ በመሆናቸው ምክንያት ውሳኔ ለመወሰን በሂደት ላይ ነን፡፡

- ከምዕራብ ጉጂ ዞን በሁለት ወረዳዎች ማለትም ደሩ ደሊፈኖ እና ጩሜ ቁራ በተከሰተ የ23 ግመሎች ሞት በደረሰን ጥቆማ መሠረት የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች በቦታዉ በመገኘት፤ የተከሰተውን የመድኃኒት ጎጂ  ባህሪያት መንስኤ ለማጣራት የክትባት ናሙና በ AUPANVAC ላብራቶሪ የተመረመረ ሲሆን በውጤቱ መሰረት ክትባቱ የጥራት ወይም የደህንነት ችግር የሌለው መሆኑን በማረጋጋጥ መንስዔው ምን እንደሆነ ሌላ ጥናት እንዲደረግበት በደብዳቤ እንዲያውቁት አድርገናል፡፡
- ከሌላ አምራች ድርጅቶች በደረሰን ጥቆማ መሰረት የአንድ አምራች ድርጅት የመድኃኒቶቹን ጥራት በመቀነስ የሚሸጥበትን ዋጋ ይቀንሳሉ ምርታቸው ከአንድ አመት በኋላ ጥራቱ እንደሚጓደል መረጃ በደረሰን መሰረት በእንስሳት መድኃኒት አምራች ድርጅቱ ከአመት በፊት የገቡ እና retain የተደረጉ ናሙናዎች ጥራት ተረጋግጦ እንዲላክልን ላቦራቶሪ ልክን ያሰራን ሲሆን በውጤቱ መሰረት መድሃኒቱ የጥራት ወይም የደህንነት ችግር የሌለውና ጥቆማው መሆኑን ማረጋጋጥ ተችሏል፡፡

### 2.3.4 ጥራትና ደህነነቱ የተረጋገጠ የእንሰሳት መኖ

**የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት**

- በዚህ በጀት አመት በአጠቃላይ ለ461 የመኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ 454 ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 98% ነው፡፡

በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን

- በበጀት አመቱ በአጠቃላይ  ለ313 በእንስሳት መኖ እና ተቋማት  ኢንስፔክሽን ማካሄድ ታቅዶ ለ244 ተካሂዳል  አፈጻጸሙ 77.95% ሆኗል፡፡ የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ዝቅተኛ የሆነው በሰሜን፣ በምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ማዕከላት በመኖ ንግድ ተቋማት ላይ መካሄድ የነበረበት ኢንስፔክሽን በተያዘው ዕቅድ መሰረት ባለመከናወኑ ነው፡፡

**ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ መኖ እና የመኖ ግብዓት**

- በዚህ በጀት ዓመት በኦንላይን በኤሌክትሮኒክስ ሲንግል ዊንዶው ለመኖና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር በአጠቃላይ ለ5500 ቶን መኖና የመኖ ግብዓት የማስገቢያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ  7320  ቶን ማከናወን በመቻሉ አፈጻጸሙ +100% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው የአስመጪዎች ቁጥር መጨመርና ጥያቄው በስፋት በመቅረቡ ነው፡፡

**የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ**

- **በአጠቃላይ በበጀት አመቱ በ130 የመኖ ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በመኖ ሬጉላቶሪ ሥራ ክፍል በቀረበው 324 ናሙናዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡**

**ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ የተመረተ የተቀነባበረ መኖ እና የመኖ**

- በዚህ በጀት አመት በአጠቃላይ 113651 ቶን የተቀነባበረ መኖና ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ገበያ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ 205370 ቶን ማከናወን በመቻሉ አፈጻጸሙ +100% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው አዳዲስ የመኖ ማቀነባሪያ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ወስደው ወደስራ በመግባታቸው ነው፡፡

**የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ**

- በዚህ 4ኛ ሩብ ዓመት በ20 የመኖ ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በመኖ ሬጉላቶሪ ሥራ ክፍል በቀረበው 241 ናሙናዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ የተቻለ ሲሆን እስከዚህ በጀት አመት 130 ታቅዶ 324 የመኖ ናሙናዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

**በቅድመ እና ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ግኝት ላይ የተወሰደ እርምጃ፡-**

- ለ3 ድርጅቶች በመጋዘናቸው ለረጅም ጊዜ ሳይወገድ የተቀመጠውን የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያስወግዱ የሚያስጠነቅቅ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ያለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የእንስሳት መኖ በማምረት ስራ ተሰማርቶ ለተገኘ አንድ ድርጅት በአጭር የጊዜ ገደብ ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አውጥቶ ወደ ህጋዊ አሰራር እንዲገባ የመጨረሻ የጥሑፍ ማስተንቀቂያ እንዲደርሰው ተደርጓል፡፡ ጉዳዩንም በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርግልን ለህግ አገልግሎት ስራ አስፈጻሚ በግልባጭ አሳውቀናል፡፡
- ለ3 የእንስሳት መኖ አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እገዳ ደብዳቤ የተጻፈ ሲሆን ከ3ቱ ድርጅቶች አንዱ ደብዳቤው ከደረሰው በኋላ ጉድለቱን በማረሙ እገዳው እንዲነሳለት በጻፈው ደብዳቤ መሰረት፣ በኢንስፔክተሮች ተረጋግጦ እገዳው ተነስቶለታል፡፡
- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ 1 ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘትያቀረበው ሰነድ ከአሰራር መመሪያው አኳያ የማያሟላ በመሆኑ ውድቅ ተደርጓል፣

- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ 1 ተቋም በቅድመ ኢንስፔክሽን ምልከታ ወቅት መመሪያውን የማያሟላ በመሆኑ ውድቅ ተደርጎ፣ በድጋሚ ተቋሙ ጉድለቱን ማስተካከላሉን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ በመጻፉ ምክንያት፣ ተቋሙን ሁለተኛ ዙር የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈልና በድጋሚ በባለሙያዎች በተደረገ የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡
- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ በመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ተቋማት ላይ በኢንስፔክተሮች በተደረገው ቁጥጥር 5 የዘይት ፋብሪካዎች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲያወጡ ተደርጓል፣
- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ መነን ፖሊስ ጣቢያ ከመኖ ጥራትና ደህንነት ጋር ተያይዞ ላቀረበው ጥያቄ ቅሬታ አቅራቢው ገዝቶ ለከብቶቻቸው ሳይመግቡት ከቀረ 7.5 ኩንታል መኖ ላይ ወካይ ናሙና በመውሰድ ናሙናውን ወደ ተቋማችን ላብራቶሪ በመላክ በላብራቶሪያችን የጥራትና ደህንነት ፍተሻ ተደርጎ የተገኘውን ውጤት የጠቅላላ አፍላቶክሲን እና የአፍላቶክሲን ቢ1 እንዲሁም ይስት ወይም ሞልድ መጠኑ የኢትዮያን የጥራት ደረጃ የማያሟላ መሆኑን ለጠያቂው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- የተለያየ የአሰራር ግድፈት የታየባቸው 5 የመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች፣ አስመጪና ላኪ ድረጅቶች የመጀመሪያ ደረጃ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፤
- 142 የተለያየ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር እንዲመዘገብ ጥያቄ ቀርቦ፣ አስፈላጊው የሰነድ ግምገማ ተካሂዶ በመኖ ምርት ምዝገባ መመሪያ ላይ ያሟላ 113 ምርት ተመዝግቦ ጊዜያዊ ሰርተፊኬት ሲሰጥ፣ 4 የምርት ዓይነት በአምራች ሀገር ገበያ ላይ የማይውል በመሆኑ ውድቅ ተደርጓል፡፡ ቀሪው 25 ምርት በምርት ግምገማ ሂደት ላይ ነው፡፡
- ለ3 ድርጅቶች በመጋዘናቸው ለረጅም ጊዜ ሳይወገድ የተቀመጠውን የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያስወግዱ የሚያስጠነቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

## 2.3.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት

- በዚህ በጀት አመት በአጠቃላይ ለ 16 የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ሥራዎችን በማጠናከር በ13 የላቦራቶሪ ምርመራ ዓይነቶች ላይ እውቅና ማግኘት ተችሏል፡

**የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ደረጃ ማሳደግ እና ማሻሻል**

- ለላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ስራዎች የሚያስፈልጉ ቋሚና አላቂ ግብዓቶችን ለሟሟላት የተለያዩ ተግባራት የተከናውኑ ሲሆን በዘህም
- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ በመደበኛ በጀት በግልጽ ጨረታ ሊገዙ የሚችሉ ግብዓቶችን የመለየትና የግዥ መግለጫ/ስፔሽፊኬሽን በማዘጋጀት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት ጨረታ የማውጣት ሥራዎች ተግባራዊ በማድረግ ከ 3 ሚሊዮን በላይ በሚገመት መደበኛ በጀት የተለያዩ አላቂ የላቦራቶሪ ግብዓት ግዥ በማከናወን በግዥ የቀረበውን የላቦራቶሪ አላቂ ግብዓቶች ትክክለኙነት በማረጋገጥ ገቢ ሆነው ለአገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

- ➢ ማዕከሉ እውቅና ያገኘባቸውን የምርመራ ዓይነቶች ለማስቀጠል እና አዳዲስ የምርመራ ዓይነቶችን ለማካተት የሚያስፈልጉ የላቦራቶሪ ቋሚ መሣሪያዎችና አላቂ ግብዓቶችን ግዥ ፍላጎት የመለየት፣ ዝርዝር የግዥ ስፔስፊኬሽን ሰነድ በማዘጋጀት ለተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ፕሮፖዛል በማቅረብ በርካታ ሥራዎች በማከናወን ከ 150 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የላቦራቶሪ ቋሚ እና አላቂ ግብዓት ግዥ በግብርና ሚ/ር ድራይቭ ፕሮጀክት ድጋፍ ተገዝተው ወደ ማዕከሉ መጋዘን ገቢ ተደርጓል።
- ➢ በተጨማሪም ለማር ምርት ጸረ- ተባይ ቅሪት ምርመራ የሚያስፈልጉ ቋሚ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን ግዥ ለማከናወን የሚያስችል ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ለግብርና ሚ/ር የምግብ ስርዓት ማጠናከሪያ ፕሮጀት ቀርቦ በጀት በማስፈቀድ 3 የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን ግዥ ለመፈጸም የሚያስችል ጨረታ እንዲወጣ በማድረግ የግዥ ሂደት ላይ ይገኛል።
- ➢ ማዕከሉ የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 8 አመታት ተከማችቶ የነበረ 8,056.5 ኪሎ ግራም የሚመዝን የላቦራቶሪው ተረፈ-ግብዓት/ውጋጅ (solid and liquid disposable laboratory waste materials) ዓይነቶችን እንደ ባህሪያቸው በመለየት፣ ክብደቱን በመለካት እና ጨረታ በማውጣት የማስወገድ ሥራ ተግባራዊ በማድረግ የሥራ አከባቢ ብክለት በመቀነስ ለሥራ ምቹ እንዲሆን ተደርጓል።
- ➢ ከምርመራ የተረፉ የእንስሳት መድኃኒቶችን የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማለፉ በፊት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከፍተኛ ድርቅ ተከስቶበት ለነበረው የምሥራቅ ቦረና ዞን ግብርና ቢሮ በኩል ለ 6 ወረዳዎች እንዲሁም በመላ አገርቷ ተንቀሳቅሶ የእንስሳት በሽታ አሰሳ እና ቅኝት ሥራዎችን ለሚያከናውን ለእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት በድጋፍ በመስጠት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

# 3. በ2017 በጀት ዓመት የነበሩ ዕድሎችና ያጋጠሙ ችግሮች

## 3.1 የነበሩ ዕድሎች

- በሁሉም ቁልፍና ወሳኝ ባለድርሻ አካላት የግብርና ቁጥጥር አስፈላጊንትን በተመለከተ እያደገ የመጣው ግንዛቤ፣
- በምርቶች ጥራትና ደህንነት ላይ የአምራቾችና የተጠቃሚዎች ግንዛቤ ማደጉ፣
- በሁለተኛው አገር በቀል ሪፎርም ለግብርና ምርቶች ጥራትና ተወዳዳሪነት በመንግስት የተሰጠው የላቀ ግምት፣
- ለዲጂታላይዜሽን አገልግሎት በመንግስት የተሰጠው ትኩረትና የባለስልጣኑን ኣአገልግሎቶች ዲጂታላይዝ ማድረግ መቻሉ፣
- ለሪፎርም ስራዎች እየተሰጡ ትኩረቶች አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል አስችለዋል።

## 3.2 ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

- ከፍተኛ የበጀት ዕጥረት
- የሰው ሀይል በቂ አለመሆንና በቁጥጥር ስራ ላይ በቂ ስልጠና አለማግኘት፣

- የቢሮ ኪራይ ውድነትና የኪራይ ጭማሪ ስጋቶች
- የተሽከርካሪ ዕጦትና ማርጀት
- የተሽከርካሪ ጥገና ወጪ ንረትና የነዳጅ ጭማሪ
- የኳረንቴን ጣቢያዎች ግንባታ ተጠናቆ ስራ አለመጀመራቸው

**4. በ2017 በዘርፉ በሁለተኛው አገር በቀል ሪፎርም የተለዩ የሪፎርም ተግባራት አፈጻጸም በግብርና ቁጥጥር የተደረጉ አስተዋጽኦ**

- በመንግስት በተወሰደው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም ምክንያት የህገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግዱ እየቀነሰ በመምጣቱ በተለይም በሚሌ እንስሳት ኳራንቲንን በኩል የሚሰጠው የቁም እንስሳት የኳረንቲን አገልግሎቶች ተደራሽ በማድረግ የቁም እንስሳትን የኤክስፖርት መጠን ማሳደግ ተችሏል። ይህም በተለይ ለተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ እና ምርታማነትና ተወዳዳሪነት መሻሻል ምክንያት ሊሆን ችሏል።ለዚህ ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ደግሞ የኳራንቲን አገልግሎት የጨረሱ እንስሳትን ከአዳማ ወደ መዳረሻ ሀገራት በባቡር ማጓጓዝ መጀመሩ ይጠቀሳል።
- የአበባን እርሻዎች ወደ ዓለማቀፍ ስታንዳርድ ለማስገባት እየተከናወኑ ያሉ የክትትል ስራዎች
- ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን የሚቀበሉ ሀገራት ቅሬታ (Notification) ለመቀነስ እየተከናወኑ ያሉ ተከታታይ ስራዎች
- ምርቶችን ጤንነትና ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ እየተክናውኑ ተግባራት ሊጠቀሱ ይችላሉ።
- የስጋ ምርቶችን እንደቻይና ላሉ ሀገራት ለመላክ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

## 4. የ2017 የ4ኛው ሩብ ዓመት የበጀት አፈጻጸም

| የበጀት ዓይነት | መለኪያ | ለ2017 የተፈቀደ በጀት | የ12 ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንዉን | አፈጻጸም በመቶኛ |
| መደበኛ | በብር | 229,622,926.06 | 222,634,852.47 | 193,555,114.50 | 86.93% |
| ካፒታል | በብር | 1,000,000.00 | 1,000,000.00 | 1,000,000.00 | 100 ዝውውር ተደርጓል |
| ድምር | | 230,622,926.06 | 223,634,852.47 | 194,555,114.50 | 87% |

# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 የ12 ወራት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በቁልፍ አመልካች

| ተራ ቁጥር | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2017 ዕቅድ | የ4ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ12 ወር ዒላማ | የ12 ወር ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በዕጽዋትና ከዕጸጽዋት ጋር በተገናኙ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ማጠናከር | | | | | | | |
| 1 | ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ | | | | | - | | |
| 2 | ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ | ቶን | 111,437 | 55,719 | 27,674 | 111,437 | 111,237 | 99.8 |
| 3 | ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ | ቶን | 2,510,360 | 451,454 | | 2,339,971 | 2,035,774 | 86.9 |
| 4 | የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 195 | 45 | 18 | 225 | 231 | 100+ |
| 5 | በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ | | | 1 | 1 | 2 | 2 | 100 |
| | ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች | | | | | | | |
| 6 | ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ሜ/ቶን | 860,000 | 215000 | 149975 | 860000 | 877750 | 100+ |

| ተራ ቁጥር | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2017 ዕቅድ | የ4ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ12 ወር ዒላማ | የ12 ወር ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ሜ/ቶን | 60,000 | 15,000 | 18200 | 60000 | 87020 | 100+ |
| 8 | የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 838 | 110 | 99 | 838 | 611 | 72.91 |
| | የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር | | | | | | | |
| 9 | በምርምር ቀርበው የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች | ቁጥር | 120 | 10 | 22 | 120 | 122 | 100+ |
| 10 | ጥራትና ዉጤታማነታቸው ተረጋግጦ የተመዘገቡና የተለቀቁ የዕፅዋት ዝርያዎች | ቁጥር | 78 | 18 | 65 | 78 | 97 | 100+ |
| 11 | በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ የአገር ውስጥ ዘር | ኩንታል | 1,527,905 | 381977 | 387,215 | 1527905 | 816891 | 53.5 |
| 12 | በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የገባ ዘር መጠን ውስጥ ለላብራቶሪ የቀረበ የናሙና ብዛት | ቁጥር | 250 | 60 | 119 | 250 | 420 | 100+ |
| 13 | በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የገባ ዘር | ኩ/ል | 509,603 | 122304 | 134,945 | 509603 | 439,003 | 86.14 |
| 14 | የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 30 | 5 | 7 | 30 | 31 | 100+ |

| ተራ ቁጥር | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2017 ዕቅድ | የ4ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ12 ወር ዒላማ | የ12 ወር ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ | | | | | - | | |
| 15 | ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ | በቁጥር | 20 | 10 | | 10<br>- | | |
| 16 | በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት | በቁጥር | 30 | 15 | | 15<br>- | | |
| | የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከር | | | | | - | | |
| | የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ | | | | | - | | |
| 17 | ደህንነቱ ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ስጋና ተረፈ ሥጋ | በቶን | 23,000 | 2500 | 4615509 | 15000 | 21200 | 100+ |
| 18 | የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት | በቁጥር | 15 | | | 15 | 15 | 100 |

| ተራ ቁጥር | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2017 ዕቅድ | የ4ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ12 ወር ዒላማ | የ12 ወር ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | ጥራቱና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ የእንስሳት ምርት ናሙናዎች | ቁጥር | 600 | 110 | 76 | 600 | 709 | 100+ |
| 20 | ለኮመርሻል የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ | ቁጥር | | 19 | 32 | 71 | 72 | 101 |
| 21 | በእንስሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | ቁጥር | 56 | 14 | 18 | 56 | 60 | 107 |
| | በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች | | | | | | | |
| 22 | ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የቁም እንስሳት | ቁጥር | 390,000 | 100000 | 170978 | 390000 | 621000 | 100+ |
| 23 | ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የለማ እንቁላል | ቁጥር | 546,000 | 137,000 | | 546000 | 4764449 | 100+ |
| 24 | ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ሰምና ማር | ቶን | 450 | 110 | 75 | 450 | 270 | 60 |
| 25 | ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ቆዳና ሌጦ | ቁጥር | 3,572,450 | 892,000 | 644027 | 3572450 | 4694016 | 100+ |
| 26 | ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል | ቁጥር | 689,090 | 172090 | 263377 | 689090 | 733662 | 100+ |

| ተራ ቁጥር | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2017 ዕቅድ | የ4ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ12 ወር ዒላማ | የ12 ወር ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 27 | ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የተሻሻለ ዳልጋ ከብት | ቁጥር | 275 | 70 | 495 | 275 | 793 | 100+ |
| 28 | ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ አባላዘር | ዶዝ | 12,000.00 | 3,000 | 1408 | 12,000.00 | 152146 | 100+ |
| | ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት | | | | | - | | |
| 29 | ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት | በቶን | 2,850 | 712.5 | 698967 | 2,850 | 3682.967 | 100+ |
| 30 | ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ የተመዘገበ የእንስሳት መድሃኒት | በቁጥር | 75 | 59 | 52 | 75 | 190 | 100+ |
| 31 | የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የተካሄደ የጥራት፣ ደህንነት እና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ | በቁጥር | 300 | 75 | 51 | 300 | 377 | 100 |

| ተራ ቁጥር | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2017 ዕቅድ | የ4ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ12 ወር ዒላማ | የ12 ወር ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 375 | 94 | 62 | 375 | 389 | 103 |
| 33 | የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 629 | 158 | 157 | 629 | 559 | 88.8 |
| | ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ | | | | | - | | |
| 34 | የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 461 | 39 | 55 | 461 | 454 | 98 |
| 35 | በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 313 | 72 | 50 | 313 | 244 | 77.95 |

| ተራ ቁጥር | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2017 ዕቅድ | የ4ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ12 ወር ዒላማ | የ12 ወር ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 36 | ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ መኖ እና የመኖ ግብዓት | ቶን | 5,500 | 1375 | 436.44 | 5500 | 7320 | 100+ |
| 37 | የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ | ቁጥር | 130 | 25 | 241 | 130 | 324 | 100+ |
| 38 | ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ የተመረተ የተቀነባበረ መኖ እና የመኖ ግብዓት | ቶን | 113,651 | 28412 | 87,686 | 85,227 | 205,370 | 100 |
| | ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የዕጽዋት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት | | | | | - | | |

| ተራ ቁጥር | የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች | መለኪያ | የ2017 ዕቅድ | የ4ኛ ሩብ ዓመት ዒላማ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም | የ12 ወር ዒላማ | የ12 ወር ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 39 | የተዘረጋ የእንስሳት የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት (ISO/IEC 17025) ትግበራ | በመቶኛ | 16 | | | 16 | 13 | 81.25 |